የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፲፫
አዲስ አበባ — ጥር ፲ ቀን ፲፱፻፺፬

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

8th Year No. 13
ADDIS ABABA - 18th January, 2002

ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፸፮/፲፱፻፺፬ ዓ.ም
የኢትዮጵያ ጤና ባለሙያዎች መማክርት ጉባኤ ማቋቋሚያ
የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ..................... ገጽ ፩ሺ፮፻፹፮

CONTENTS

Council of Ministers Regulations No. 76/2002
Ethiopian Health Profesionals Council Establishment
Council of Ministers Regulations ................. Page 1686

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፸፮/፲፱፻፺፬
### ስለኢትዮጵያ ጤና ባለሙያዎች መማክርት ጉባኤ መቋቋም
### የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ በተደነገገው መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል ።

#### ክፍል ፩
#### ጠቅላላ

፩· **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ጤና ባለሙያዎች መማክርት ጉባኤ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፸፮/፲፱፻፺፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ፡

፩· "የጤና ሙያ" ማለት ማንኛውም የሕክምና ፣ የፋርማሲ፣ የነርስ ፣ የጤና ረዳት የቴክኒሻኖች እና ማንኛውንም የጤና አጠባበቅ ሙያን ያጠቃልላል ፤

፪· "የጤና ባለሙያ ማህበር" ማለት እያንዳንዱን የጤና ሙያ ዘርፍ የሚወክል ሕጋዊ ማህበር ነው ፤

፫· "የጤና ተቋም" ማለት ሆስፒታል ፣ ጤና ጣቢያ ፣ ክሊኒክ ፡ ፋርማሲ ወይም ጤና ነክ አገልግሎት የሚሰጥ ሆኖ በሽታን የመከላከል ተግባር የሚያከናውንና በማስከፈል ወይም በነፃ የማከም የማዳን አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ነው ፤

፬· "የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት" ማለት የጤና ወይም ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎቶችን ለማበርከት እንዲቻል የሚሰጥ የሙያ ፈቃድ ነው ፤

፭· "ሚኒስቴር" ወይም ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው ።

### *COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS No. 76/2002*
### *ETHIOPIAN HEALTH PROFESSIONALS COUNCIL ESTABLISHMENT COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS*

#### *PART I*
#### *General*

1. *Short Title*

These Regulations may be cited as the "Ethiopian Health Profesionals Council Establishment Council of Ministers Regulations No. 76/2002."

2. *Definition*

In these Regulations unless the context otherwise requires:

1) "Health Profession" means any medical, pharmacy, nursing health assistance technicians and any other health related field of study;
2) "Health Profession Association" means a legally recognized association which represents the respective branch of health profession;
3) "Health Institution" means hospital, health centre, clinic, pharmacy or a health related institute that renders preventive medicine and gives curative treatment either by charging fees or for free;
4) "Professional Competence Confirmation Certificate" means a professional licence which entitles to provide medical or other health related services.
5) "Ministry" or Minister" means the Ministry or Minister of Health, respectively.

ያንዱ ዋጋ 3·40
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

## ክፍል ፪
## ስለጤና ባለሙያዎች መማክርት ጉባኤ
### ንዑስ ክፍል ፩
### የጤና ባለሙያዎች መማክርት ጉባኤ መቋቋም

፫· *መቋቋም*

ተጠሪነቱ ለሚኒስትሩ የሆነ የኢትዮጵያ ጤና ባለሙያዎች መማክርት ጉባኤ (ከዚህ በኋላ "ጉባኤው" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ መሠረት ተቋቁሟል ።

፬· *የጉባኤው ሥልጣንና ተግባር*

ጉባኤው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል ፤

፩· በዚህ ደንብ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ሚኒስትሩን ያማክራል ፤
፪· በሀገሪቱ ውስጥ የሚሰጠውን የጤና ባለሙያዎች ሥልጠና ጥራት ባለው ሁኔታ እንዲካሄድ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል ፤
፫· የሙያ ሥነምግባር በባለሙያዎች መተግበሩን ያረጋግጣል ፤
፬· በሀገሪቱ ውስጥ በየጊዜው የሚመዘገቡትና በልዩ ልዩ ምክንያቶች ከመዝገብ የሚሠረዙት ባለሙያዎች ስም ዝርዝር በጽሕፈት ቤቱ በትክክል መያዙን ይከታተላል ፤ ይቆጣጠራል ፤
፭· የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴን አሠራር ይቆጣጠራል ፤
፮· በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፬(፪) ፤ አንቀጽ ፲፭(፩) እና (፪) ፤ አንቀጽ ፲፮(፬) መሠረት የሚቀርብለትን እንዲሁም የሚኒስቴሩን ውሣኔ የሚጠይቁ ጉዳዮችን በመመርመርና የበኩሉን ሃሣብ በማከል ለሚኒስቴሩ ውሳኔ እንዲቀርብ ያደርጋል ፤
፯· በሚኒስትሩ የሚመሩለትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል ።

፭· *ስለጉባኤው አባላት*

ጉባኤው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል ፤

፩· የክልል መስተዳድር ጤና ቢሮ ወይም ቀጥታ ተጠሪነቱ ለፌዴራሉ መንግሥት የሆነ የከተማ መስተዳድር ጤና ቢሮ አንዳንድ ተወካዮች ............................ አባል
፪· ከሚከተሉት የሚኒስቴሩ መ/ቤት አካላት የተውጣጡ ተወካዮች፡ ........................................................ "
  ሀ) የጤና አገልግሎትና ስልጠና መምሪያ ኃላፊ .................................................... "
  ለ) የጤና ባለሙያዎች ትምህርትና ሥልጠና ቡድን አንድ ተወካይ ...................................... "
  ሐ) የጤና ባለሙያዎች ደረጃ ምደባና ግምገማ ቡድን አንድ ተወካይ ............................ "
  መ) የጤና አገልግሎት ቡድን አንድ ተወካይ ........................................................ "
  ሠ) የሕግና ሜዲኮሌጋል አገልግሎት አንድ ተወካይ ........................................................ "
  ረ) አንድ የቀዶ ሕክምና ሙያ እስፔሻሊስት ተወካይ ........................................................ "
  ሰ) አንድ የውስጥ ደዌ ሕክምና ሙያ እስፔሻሊስት ................................................ "
፫· ከሚከተሉት የጤና ባለሙያዎች ማኅበራት የተውጣጡ ተወካዮች ፤
  ሀ) የሐኪሞች ማህበር ሁለት ተወካዮች ....... አባል
  ለ) የጤና አጠባበቅ ባለሙያዎች ማህበር አንድ ተወካይ .................................................... "
  ሐ) የፋርማሲስቶች ማህበር ሁለት ተወካዮች ................................................ "
  መ) የነርሶች ማህበር ሁለት ተወካዮች ............. "
  ሠ) የጤና ረዳቶች ማህበር አንድ ተወካይ ........... "
  ረ) የላቦራቶሪ ቴክኒሽያኖች ማህበር አንድ ተወካይ ................................................ "
  ሰ) የራዲዮግራፊ ቴክኒሽያኖች ማህበር አንድ ተወካይ ................................................ "

## PART 2
## *Health Professionals Council*
### *Sub-Section 1*
### *Establishment of Health Professionals Council*

3. *Establishment*

The Ethiopian Health Professionals Council (herein after refered to as the "Council") is hereby established by these Regulations.

4. *Powers and Duties of the Council*

The Council shall have the following powers and duties:

1) advise the Minister on matters provided in these Regulations;
2) work in collaboration with the appropriate bodies, to ensure that health professional trainings offered in the country are of high standard;
3) make sure that professional ethics is observed by professionals;
4) follow up and supervise that the names of registered professionals and those who are cancelled from the registry due to various reasons are properly kept by the secretariat;
5) supervise the performance of the Executive Committee;
6) examin and submit to the Ministry matters directed to it in accordance with Articles 14 (2), 15 (1) and (2), and 16 (4) of these Regulations and those matters that need to be decided by the Ministry along with its opinion.
7) perform other matters directed to it by the Minister.

5. *Members of the Council*

The council shall have the following members:

1) regional health offices or health offices of city administrations directly accountable to the Federal Government, each represented by one representative ........................................................ Member
2) representatives selected from the following organs of the Ministry:
   (a) Health Service and Training Department Head ............................. Member
   (b) a representative of Health Professionals Education and Training Team ........................................................ "
   (c) a representative of Health Professionals Standardization and Evaluation Team ......... "
   (d) a representative of Health Services Team ........................................................ "
   (e) a representative of Legal and Medico Legal Service ............................................ "
   (f) a surgical specialist ........................................ "
   (g) one internal medicine specialist ........ Member
3) Representatives selected from the following health professionals associations:
   (a) two representatives of the Ethiopian Medical Association ........................................ "
   (b) a representative of the Ethiopian Public Health Professionals Association ................. "
   (c) two representatives of the Pharmacy Association ........................................................ "
   (d) two representatives of the Ethiopian Nurses Association ........................................ "
   (e) a representative of the Health Assistants Association ........................................................ "
   (f) a representative of the Laboratory Technicians Association ................................ "
   (g) a representative of the Radiography Technicians Association ............................ "

፬· የመድኃኒት አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን
አንድ ተወካይ .................................................. ”
፭· የትምህርት ሚኒስቴር ተወካዮች ........................ ”
፮· ከላይ የተደነገገው ቢኖርም ፡ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘና ፈቃደኛ ከሆኑ አግባብነት ያላቸው ሌሎች አካላትም በአባልነት ሊወከሉ ይችላሉ ፡፡

፮· የጉባኤው አባል ለመሆን የሚያስፈልጉ መስፈርቶች

ማንኛውም የጉባኤው አባል የሚከተሉትን መመዘኛዎች ማሟላት አለበት ፡

፩· የዕፅሱስ ያልተጠናወተው፡
፪· የአልኮል ሱሰኝነት ያልተቆራኘው ፡
፫· የጤና ባለሙያ ከሆነ በሙያው የተመዘገበ ፡
፬· በሥነ–ምግባሩ የተመሰገነ ፡
፭· በአዕምሮው ጤነኛ የሆነና ፡
፮· ከሙያው ጋር በተዛመደ ወንጀል ተከሶ ያልተፈረደበት ፡፡

፯· ከጉባኤው አባልነት ስለመነሳትና የጎደሉትን ስለመተካት

፩· አንድ የጉባኤው አባል በሚከተሉት ምክንያቶች ከአባልነት ሊነሳ ይችላል ፡
ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ መሠረት ከተጠቀሱት መመዘኛዎች ውስጥ አንዱን ሳያከብር ሲቀር ወይም ፡
ለ) ያለምንም ፈቃድ ወይም አስቀድሞ ባለማሳወቅ ከሁለት ተከታታይ መደበኛ ስብሰባዎች ቀሪ ሲሆን እና በጽሑፍም ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ሳያሻሽል ሲቀር ፡፡
፪· በአንድ የጉባኤ አባል ከአባልነት መነሳት ምክንያት ክፍተት ሲፈጠር አባሉን መርጦ የላከው አካል ምትክ አባል መርጦ መላክ አለበት ፡፡

፰· ስለጉባዔው የአሠራር ሥነ–ሥርዓት

፩· ጉባኤው የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ያወጣል፡፡
፪· ከአባላቱ ከግማሽ በላይ ሲገኙ ምልዐተ ጉባኤ ይኖራል ፡፡
፫· እያንዳንዱ ውሳኔ በድምፅ ብልጫ የሚያልፍ ሲሆን ፡ እኩል በኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል ፡፡
፬· የጉባኤው መደበኛ ስብሰባ በዓመት ፬ ጊዜ ይካሄዳል ፡፡ ሆኖም እንደአስፈላጊነቱ ከጉባኤው አባላት ከግማሽ በላይ የሆኑት ሲስማሙ የጉባኤው ሰብሳቢ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል ፡፡
፭· የጉባኤው አባላት የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል፡፡

፱· ስለጉባኤው አካላት

ጉባኤው የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል ፡
ሀ) የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ፡
ለ) የትምህርትና ሥልጠና ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ፡
ሐ) የሙያ ሥነምግባር ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ ፡
መ) የምዝገባና የሙያ ፈቃድ ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ ፡
ሠ) ጽሕፈት ቤት ናቸው ፡፡

ንዑስ ክፍል ፪
ስለ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ

፲· ስለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው አባላት

፩· የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል ፡
ሀ) የጉባኤው ሊቀመንበር ...................... ሰብሳቢ
ለ) የጉባኤው ም ሊቀመንበር ............. ም ሰብሳቢ
ሐ) የጤና ባለሙያዎች ትምህርትና ሥልጠና ቡድን አንድ ተወካይ ......................... አባል
መ) የጤና ባለሙያዎች ደረጃ ምደባና ግምገማ ቡድን አንድ ተወካይ ............................ ”
ሠ) የጤና አገልግሎት ቡድን አንድ ተወካይ ...... ”
ረ) የሦስቱ ንዑሳን ኮሚቴ ሰብሳቢዎች ........... ”
ሰ) የሕግና ሜዲኮሌጋል አገልግሎት አንድ ተወካይ ....................................................... ”
ሸ) የመድኃኒት ቁጥጥርና አስተዳደር ባለሥልጣን አንድ ተወካይ ............................ ”
ቀ) የነርሶች ማህበር አንድ ተወካይ ................. ”
በ) የተዛማጅ ሙያ አንድ ተወካይ ..................... ”

4) A representative of the Drug Administration and Control Authority........................................ member
5) Two representatives of the Ministry of Education ................................Member
6) Notwithstanding to the above provisions and when it is deemed necessary, other appropriate organs may also be represented if they are willing to do so.

6. *Criteria to be Member of the Council*

Any member should fulfil the following criteria:
1) Should be free from substance addiction;
2) should be free from alcoholism;
3) if he/she is a health profesional should be a registered professional;
4) should be ethically commendable;
5) should be mentally healthy; and
6) not criminally accused and convicted in relation with his profession.

7. *Removal and Substitution of Council Members*

1) A member may be removed from the council membership for the following reasons:
(a) if he/she fails to fulfill any one of the criteria set under Article 6 of these Regulations
(b) failure to be present at two consecutive meeting without any permission or prior notification and who fails to improve conduct following a written warning.
2) whenever a council member is removed from membership, the organ who selected and sent the member shall send a substitute.

8. *Work Procedures of the Council*

1) the council shall adopt its own rules of procedure.
2) there shall be a quorum if more than half of the members are present.
3) every decision shall be endorsed by a majority vote, and if the meeting gets tied then the chairman shall have a casting vote.
4) the regular meeting of the council shall be made four times a year, however, when deemed necessary the chairman may call extra ordinary meeting upon the decision of more than half of the members of the council.
5) the term of office of members of the council shall be five years.

9. *Organs of the Council*

The council shall have the following organs:
(a) Executive committee;
(b) Education and Training sub-committee;
(c) Professional ethics sub-committee;
(d) Registration and Professional license sub-committee;
(e) Secretariat.

*Sub-Section 2*
*Executive Committee*

10. *Members of the Executive Committee*

1) The Executive Committee consists of the following members:
(a) Chairman of the Council .................Member
(b) Vice Chairman of the Council.................... ”
(c) a representative of Health Professional Training and Education Team ................. ... ”
(d) a representative of Health Professionals Standardization and Evaluation Team ........................................................... ”
(e) chairman of the three sub-committes .......... ”
(f) a representative of the Legal and Medicolegal Service.................................... ”
(g) a representative of Drug Administraiton and Control Authority ............................... ”
(h) a representative of the Ethiopian Nurses Association.................................... ”
(i) a representative of related professions................................................... ”

፪· የጉባኤው ሰብሳቢና ም/ሰብሳቢ ከጉባኤው አባላት መካከል በሚኒስትሩ ተመርጠው ይሾማሉ ።

፫· የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት የሚመረጡት ከጉባኤው አባላት መካከል ይሆናል ።

፬· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ሌሎች አባላትም በኮሚቴው ሊወከሉ ይችላሉ ።

፲፩· ስለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ሥልጣንና ተግባር

የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል ፡

፩· ንዑሳን ኮሚቴዎችን ያቋቁማል ፣ ሥራቸውን ያስተባብራል፡ ይቆጣጠራል ፣

፪· በዚህ ደንብ መሠረት የሚተላለፉ ውሳኔዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ያረጋግጣል ፣

፫· የጉባኤውን ውሳኔዎች ያስፈጽማል ፡

፬· ጉባኤው በማይሰበሰብበት ጊዜ እርሱን ተክቶ ይሠራል። ሆኖም ጉባኤው የወሰናቸውን ውሳኔዎች ለማገድ ወይም ለመለወጥ አይችልም ፣

፭· የጉባኤውን የዕለት ተዕለት ተግባራት ያከናውናል ፡

፮· ከጉባኤው የሚመሩለትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

፲፪· ስለ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የአሠራር ሥነ-ሥርዓት

፩· የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የራሱ የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ይኖረዋል ።

፪· የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው እንደአስፈላጊነቱ ይሰበሰባል ።

፫· ከአባላቱ ከግማሽ በላይ ሲገኙ ምልዐተ ጉባዔ ይኖራል።

፬· እያንዳንዱ ውሳኔ በድምጽ ብልጫ የሚያልፍ ሲሆን፣ ድምፅ እኩል በእኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።

፭· የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል።

ንዑስ ክፍል ፫
ስለ ንዑሳን ኮሚቴዎች

፲፫· ስለንዑሳን ኮሚቴዎች አባላት ጥንቅርና የሥራ ዘመን

፩· የእያንዳንዱ ንዑሳን ኮሚቴ አባላት ከጉባዔው አባላት መካከል ይመረጣሉ።

፪· የንዑስ ኮሚቴ አባላት የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል።

፲፬· የትምህርትና ሥልጠና ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር

ንዑስ ኮሚቴው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

፩· በሕክምና ሙያ ሥርዓተ ትምህርት የአቀራረጽና የማሻሻል ሂደት በመሳተፍ የራሱን ሀሳብ ያቀርባል፤

፪· የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ፈተና ይሰጣል፤ ውጤቱንም ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ይልካል፤

፫· በዚህ ደንብ መሠረት የተላለፉ ውሳኔዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፤

፬· ስለሥራው ከንዋኔ ወርሀዊ ሪፖርት ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ያቀርባል፤

፭· ስለሥራው ዕድገትና መሻሻል ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ሀሳብ ያቀርባል፤

፮· ተግባርና ኃላፊነቱን በተገቢው ሁኔታ ለመወጣት ይችል ዘንድ ቡድኖችን ለማቋቋም ይችላል፤

፯· ሌሎች በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።

2) The chairman and vice-chairman of the council shall be elected and appointed by the Minister from among members of the council.

3) Members of the executive committee shall be elected from among the members of the council.

4) Notwithstanding to the provisions of Sub-Article (1) of this Article, other members may also be represented in the committee if it is found necessary.

11. *Powers and Duties of the Executive Committee*

The Executive Committee shall have the following powers and duties:

1) establish sub-committees, coordinate and supervise their work:

2) ensure whether the decisions passed as per these regulations are implemented:

3) execute the decisions of the council;

4) shall represent and run the duties of the council at the time when the council is not in-session: it cannot, however, suspend or reverse the decisions of the council.

5) carry out the day to day activities of the council.

6) perform such other matters as are directed to it by the council.

12. *Meetings of the Executive Committee*

1) The Executive Committee shall adopt its own rules of procedure;

2) The Executive Committee shall be convened as may be necessary;

3) There shall be a quorum when more than half of the members of the Executive Committee are present at its meetings.

4) Each decision shall be endorsed by a majority vote, in case of a tie, however, the chaiman shall have a casting vote;

5) The term of office of the Executive Committee shall be five years.

SECTION 3
*Sub-Committees*

13. *Composition and Terms of the Sub-Committees*

1) Each sub-committee members shall be elected from among the members of the council;

2) The term of the sub-committee members shall be five years;

14. *Powers and Duties of Education and Training Sub-Committee*

The sub-commitee shall have the following powers and duties:

1) participate in the preparation and amendment process of the curriculum of the medical profession and forward its opinion thereof.

2) give professional competence confirmation examination and submit the results to the Executive Committee;

3) Implement decisions passed according to these regulations;

4) submit monthly report of its performance to the Executive Committee;

5) forward its opinion to the Executive Committee on the progress and improvement of its work;

6) may form teams to carry out its powers and duties properly;

7) perform such other duties that may be directed to it by the Executive Committee.

፲፭· <u>የምዝገባና የሙያ ፈቃድ ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር</u>

ንዑስ ኮሚቴው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

፩· ለምዝገባና ለሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚቀርቡ ማመልከቻዎችንና ተያይዘው የሚቀርቡ ማስረጃዎችን መርምሮ የምርመራውን ውጤት ከውሳኔ ሀሳብ ጋር ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ያቀርባል፤

፪· የሙያ ፈቃድ መስፈርቶችን በየደረጃው አዘጋጅቶ ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ያቀርባል ፤

፫· ስለሥራው ክንዋኔ ወርሀዊ ሪፖርት ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ያቀርባል፤

፬· ስለሥራው ዕድገትና መሻሻል ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ሀሳብ ያቀርባል ።

፭· ተግባርና ኃላፊነቱን በተገቢው ሁኔታ ለመወጣት እንዲችል ቡድኖችን ለማቋቋም ይችላል።

፲፮· <u>የሙያ ሥነ ምግባር ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር</u>

ንዑስ ኮሚቴው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

፩· የጤና ሙያ የሚጠይቀው ሥነ ምግባር ባለመከበሩ በባለሙያ ላይ የሚቀርብ ክስን ተቀብሎ ምርመራ ያካሂዳል፣ ጉዳዩን ያጣራል ፤

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚቀር በውን ክስ ለማየት በቂ ማስረጃ መኖሩን ካረጋገጠ፣ መልሱን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ይዞ እንዲቀርብ በመግለጽ ክሱን ክስ ለቀረበበት ባለሙያ ይልካል፣

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችሉ ማስረጃ ዎችን ይሰበስባል፣

፬· በባለሙያ ላይ የቀረበውን ክስና ማስረጃ እንዲሁም በባለሙያው የተሰጠውን መልስና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ የምርመራውን ውጤት ከቅጣት ሃሳብ ጋር ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ያቀርባል፣

፭· ስለሥራው ክንዋኔ ወርሀዊ ሪፖርት ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ያቀርባል፣

፮· ተግባርና ኃላፊነቱን በተገቢው ሁኔታ ለመወጣት እንዲችል ቡድኖችን ለማቋቋም ይችላል፤

፯· ሌሎች በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።

፲፯· <u>የንዑስ ኮሚቴ የአሠራር ሥነ ሥርዓት</u>

፩· እያንዳንዱ ንዑስ ኮሚቴ እንደአስፈላጊነቱ ስብሰባ ይኖረዋል።

፪· ከእያንዳንዱ ንዑስ ኮሚቴ አባላት ከግማሽ በላይ ሲገኙ ምልዐተ ጉባዔ ይኖራል።

፫· የእያንዳንዱ ንዑስ ኮሚቴ ውሳኔ በድምጽ ብልጫ ያልፋል፤ እኩል በእኩል የተከፈለ ድምጽን በተመለከተ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።

፬· በዚህ አንቀጽ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ እያን ዳንዱ ንዑስ ኮሚቴ የራሱን የአሠራርና የስብሰባ ሥነ ሥርዓት መመሪያ አውጥቶ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሲያፀድቀው ሊሠራበት ይችላል።

<u>ንዑስ ክፍል ፬</u>

<u>ስለ ጉባዔው ጽሕፈት ቤት</u>

፲፰· <u>ስለጉባዔው ጽሕፈት ቤት መቋቋም</u>

ጉባዔው ከሚኒስቴሩ መሥሪያ ቤት በሚኒስትሩ ተመርጠው በሚመደቡ ሬጅስትራር፣ ምክትል ሬጅስትራር የሚመራና የዕለት ተዕለት የጽ/ቤት ተግባራት የሚያከናውን ጽ/ቤት ይኖረዋል።

15. *Powers and Duties of Registration and Profesional License Sub-Committee*

The sub-committee shall have the following powers and duties:

1) verify applications and the documents attached thereto that are submitted for registration, professional competence confirmation certificate and submit the result along with its opinion to the Executive Committee.
2) set the criteria for a professional license of the respective standard and submit same to the Executive Committee.
3) submit to the Executive Committee monthly report of its performance.
4) forward its opinion on the progress and improvement of its work to the Executive Committee.
5) May form teams to carry out its powers and duties properly.

16. *Powers and Duties of Profesional Ethics Sub-Committee*

The sub-committee shall have the following powers and duties.

1) It shall conduct investigation where complaints are lodged on the non-observance of a professional ethics;
2) If it finds sufficient evidence to support the complaint submitted as per Sub-Article (1) of this Article, it may instruct the professonal, against whom the complaint is lodged, to come up with a defense in one month time.
3) Collect evidence that may help it to implement the powers and responsibilities vested in it by Sub-Article (1) of this article.
4) Having examined the complaint brought up against the professional and the statement of defense and evidence submitted thereby submit its finding to the Executive Committee along with a proposed punishment;
5) Submit to the Executive Committee a monthly report of its performance;
6) May form teams to carry out its duties and responsibilities properly.
7) Perform such other duties that may directed to it by the Executive Committee.

17. *Meetings of a Sub-Committee*

1) each sub-committee may have meetings as it is deemed necessary.
2) there shall be a quorum when more than half of the members of each sub-committee are present at its meetings.
3) the decision of each sub-committee shall be passed by a majority vote of members present at the meeting. In case of a tie the chairman shall have a casting vote.
4) without prejudice to the provisions of this Article each sub-committee shall adopt its own rules of procedure which will be operative when it is endorsed by the Executive Committee.

*Sub-Section 4*

*The Secretariat of the Council*

18. *Establishment of the Secretariat of the Council*

The Council shall have a secretariat which will be run by a Registrar and Deputy Registrar to be elected and appointed by the Minister from the Ministry to deal with day to day activities.

፲፱· ስለጉባዔው ጽ/ቤት ተግባራት

የጉባዔው ጽ/ቤት የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፣

፩· የሙያ ችሎታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጣቸውን ባለሙያዎች ስምና የሙያ ደረጃ እንዲሁም ሌሎች አግባብ ያላቸው መረጃዎች መዝግቦ ይይዛል፣ መዝገቡም ለሕዝብ ክፍት ይሆናል፣ እንዲሁም ዝርዝሩ በየዓመቱ በመንግሥት ጋዜጣ እንዲወጣ ያደርጋል።

፪· በሞት፣ ሞያውን በመተው፣ በወንጀል ቅጣት፣ በሥነ ምግባር ጉድለት ውሣኔዎች ወይም በመሳሰሉት ምክን ያቶች ባለሙያዎች የሚሰጡት አገልግሎት ሲቋረጥ መዝግቦ ይይዛል፣

፫· ለምዝገባና ለሙያ ችሎታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚቀርቡ ማመልከቻዎችንና የባለሙያዎችን ሰነዶች ከሚኒስቴሩ ሲመራለት ለምዝገባና ለሙያ ፈቃድ ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ ያቀርባል።

፬· ሌሎች ከምዝገባ ጋር የተዛመዱ ተግባራትን ያከናውናል፣

፭· የትምህርትና የሥነ ምግባር ጉዳዮችን ይቀበላል፣ ለተፈጻሚነታቸውም ጉዳዩ ለሚመለከተው ኮሚቴ ይመራል፣

፮· እንደአግባቡ ከሚኒስቴሩና ከጉባዔው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## ክፍል ፫

## ስለሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ምዝገባ

፳· ስለሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አስፈላጊነት

ማንኛውም የጤና ባለሙያ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሊኖረው ይገባል።

፳፩· የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ

፩· የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ ጥያቄ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በሚዘጋጅ ፎርም ተሞልቶ መቅረብ አለበት።

፪· አመልካቹ ከማመልከቻው ጋር የሚከተሉትን ኦሪጂናል ሰነዶች አያይዞ ማቅረብ አለበት፣

ሀ) ሥልጠና ከወሰደበት የትምህርት ተቋም የሚቀርብ የትምህርት ማስረጃ፣

ለ) እንደአስፈላጊነቱ በልምምድ (ኢንተርንሺፕ) ፕሮግራም ውስጥ ካለፈበት ተቋም የሚቀርብ ማስረጃ፣

ሐ) ሚኒስትሩ በሚወስነው መሠረት የሙያ ብቃት ፈተና መውሰድ ያለባቸውን በተመለከተ ይህንኑ ፈተና ማለፋቸውን የሚያሳይ ማስረጃ፣

መ) እንደአስፈላጊነቱ በሚኒስትሩ የሚጠየቁ ሌሎች ሰነዶች፣

፫· አመልካቹ ለሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አግባብ ባለው ደንብ የተወሰነውን ክፍያ ይከፍላል።

፳፪· የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለማሳደስ

፩· የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በየአምስት ዓመቱ መታደስ አለበት፣

፪· የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማሳደስ የሚፈልግ ማንኛውም ባለሙያ የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፣

ሀ) የምስክር ወረቀቱ ጊዜ ከማለቁ ከአንድ ወር በፊት ማመልከቻ የማቅረብ፣

ለ) የሙያ ሥነ ምግባር መለኪያዎችን የማሟላት፣

ሐ) እንደአስፈላጊነቱ በጉባዔው የሚሰጠውን ፈተና የማለፍ፣

መ) የማሳደሻ ክፍያ የመክፈል።

19. *Duties of the Secretariat*

The secretariat of the council shall have the following duties:

1) register and keep the names, their professional standard, and other necessary documents of the professional to whom a professional competence confirmation certificate is given. The register shall be open to the public and the list shall be published yearly in a state-owned newspaper.
2) register and keep the names of those profesionals who have terminated their service due to death, quitting the profession, a criminal sentence, a decision on ethical non-observance or other similar grounds.
3) submit to the registration and licence sub-committee applications for registration and professional competence confirmation certificate that are directed to it by the Minister.
4) perform other duties related to registration.
5) receive educational and ethical matter and direct it to the appropriate committee for its execution.
6) perform other duties directed to it by the Ministry and the Council.

## PART 3

## *Registration of Professional Competence Confirmation Certificate*

20. *The Necessity of Professional Competence Confirmation Certificate*

Every health professional should have a professional competence confirmation certificate.

21. *Application for Professional Competence Confirmation Certificate*

1) the application for professional competence confirmation certificate shall be submitted in the form prepared in accordance with the directives of the Ministry.
2) the applicant should attach with his application the following original documents:
   (a) credentials from institutions of training.
   (b) documents given by an institute in evidence of completing an internship programme.
   (c) concerning professionals who, upon the decision of the Minister, are required to take professional competence confirmation examination, document to the effect of testifying that one has passed such an examination.
   (d) other documents that may be required by the Minister.
3) The applicant shall pay the license renewal fee determined by the appropriate Regulations.

22. *Renewal of Professional Competence confirmation Certificate*

1) the professional competence confirmation certificate should be renewed every five years.
2) any professional who wants to renew the professional competence confirmation certificate shall fulfil the following:
   (a) submit an application one month before the certificate expires;
   (b) fulfill professional ethics criteria;
   (c) should pass the examination that may be given by the council when necessary;
   (d) pay renewal fees.

፳፫· <u>የሙያ ፈቃድ ስለማገድ ወይም ስለመሠረዝ</u>

ይህን ደንብ ወይም በዚህ ደንብ መሠረት የሚወጡ የጤና ባለሙያ ስነምግባር መመሪያዎችን የጣሰ ጤና ባለሙያ እንደሁኔታው ፈቃዱ ይታገዳል ወይም ይሰረዛል።

## <u>ክፍል ፬</u>

## <u>ስለሚኒስትሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

፳፬· <u>ስለሚኒስትሩ ሥልጣን</u>

፩· ሚኒስትሩ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬(፮) መሠረት የሚቀርቡለትን ጉዳዮች ከመረመረ በኋላ፣

ሀ) የውሳኔ ሃሳቡን ለማጽደቅ ወይም የራሱን የተለየ ውሳኔ ለመስጠት፣

ለ) በአግባቡ ያልተጣራ ወይም ያልተጤነ ጉዳይ ካለ ሁኔታው እንደገና ተጣርቶ ከውሳኔ ሃሳብ ጋር እንዲቀርብ ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው እንዲመለስ ለማድረግ ይችላል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ለ) መሠረት ለሁለተኛ ጊዜ በሚመለከተው ንዑስ ኮሚቴ የታየን ጉዳይ በተመለከተ ሚኒስትሩ የሚያሳልፈው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል።

፫· ጉባዔው በሚያቀርብለት የውሳኔ ሃሳብ መሠረት ሚኒስትሩ ከሚከተሉት በአንዱ እንደሁኔታው ለተወሰነ ጊዜ ፈቃዱን ሊያግድ ይችላል፣

፩· ሳይመዘገብ ወይም የሙያ ፈቃዱን ሳያሳድስ የጤና ባለሙያነት ተግባር ሲሰራ ቢገኝ፣

፪· በተሰጠው የሙያ ፈቃድ መነሻ በኃላፊነት በከፈተው የጤና ተቋም ውስጥ በዚህ ደንብ በተጠቀሱት ምክንያቶች የሙያ ፈቃዱ የታገደበት ወይም የተሰረዘበትን ወይም የሙያ ፈቃድ ጨርሶ የሌለውን የጤና ባለሙያ ሲያሠራ የተገኘ እንደሆነ፣

፫· በአንቀጽ ፳፬ ንዑስ አንቀጽ (፬)(ሀ)-(መ) የተጠቀሰው ህገወጥ ተግባር ለፍ/ቤት ወይም ለጉባዔው ቀርቦ ውሳኔ እስኪወሰን ድረስ፣

ይሁንና በአንቀጽ ፳፬ ንዑስ አንቀጽ ፫(፫) የተጠቀሰው ተግባር የሚታየው በሚኒስትሩ ወይም በጉባዔው ወይም በንዑስ ኮሚቴው ከሆነ እገዳው በ፮ ወር ጊዜ ውስጥ ውሣኔ ማግኘት አለበት።

፬· በአንቀጽ ፳፫ የተጠቀሰው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ፣ ጉባዔው በሚያቀርብለት የውሳኔ ሃሳብ መሠረት ሚኒስትሩ ከዚህ በሚከተሉት ሁኔታዎች በአንዱ ፈቃዱን ሊሰርዝ ይችላል፣

ሀ) ፈቃዱ የተገኘው በሐሰት ማስረጃ አማካይነት ለመሆኑ በሚመለከተው አካል በማስረጃ ሲረጋገጥ፣

ለ) ለጤና ባለሙያነት ብቃት የሌለው መሆኑን በሚያሣይ ከባድ የወንጀል ድርጊት ተከሶ ጥፋተኛነቱ የተረጋገጠ እንደሆነ፣

ሐ) ሆነብሎ የጤና ባለሙያነት ስነምግባርን በሚቃረን ሁኔታ ከተሰጠው ደረጃ በላይ ሲሠራ የተገኘ እንደሆነ፣

መ) ከጤና ባለሙያነቱ በታገደበት ወቅት ህገወጥ ጥቅም ለማግኘት ሲል የጤና ባለሙያነት አገልግሎት መስጠቱ ተረጋግጦ በተደጋጋሚ በጽሑፍ የተሰጠውን ማስጠንቀቂያና የእገዳ ውሳኔ ጥሶ ሲሠራ የተገኘ እንደሆነ፣

፭· የአንቀጽ ፲፱ ንዑስ አንቀጽ (፪) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ፣ በወንጀል ቅጣትና በሥነምግባር ጉድለት ውሳኔዎች በእገዳም ሆነ በመሠረዝ ምክንያት አገልግሎት ሲቋረጥ የተያዘ መዝገብ ለሕዝብ ክፍት ይሆናል። በመንግሥት ጋዜጣም በ፵፰ ሰዓት ውስጥ እንዲወጣ ይደረጋል።

፮· ሚኒስትሩ ለዚህ ደንብ አፈጻጸም የሚረዱ የጤና ባለሙያ ሥነ ምግባር መመሪያዎችን ለማውጣት ይችላል።

23. *Suspension or Cancellation of Professional Licence*

The professional licence of any health professional who violates these regulations or directives on health professional ethics issued under these regulations shall be suspended or cancelled, as the case may be.

## PART 4

## *Powers and Duties of the Minister*

24. *Powers of the Minister*

1) having examined matters submitted to him in accordance with Article 4 (6) of these regulations, the Minister:
   (a) may uphold the proposed decision or render a different decision,
   (b) may direct the case to the appropriate sub-committee so that the case may be re-examined and submitted with a proposed decision when it is believed that the case has not been examined properly.
2) the decision of the Minister shall be final with respect to cases re-examined by the appropriate sub-committee for the second time persuant to Sub-Article (1) (b) of this Article.
3) based on the proposed decision submitted by the council the Minister may suspend the licence for a specified period of time on one of the following grounds:-
   1) when it is found that one has been performing as a health professional without registration or renewing the licence.
   2) if found employing a health professional whose license has been suspended or cancelled for violating these regulations or who does not even have a professional licence, in the health institution for which one is responsible and opened based on one's professional license.
   3) until a court or the council decision is passed on the above mentioned illegal act under Article 24 Sub-Article 4(a-d).
   But if the case which is mentioned under Article 24 Sub-Article 3.3 will be seen by the Minister, or by the council or the sub-committee the suspension must be decided within 6 months.
   4) without prejudice to what is generally stated in Article 23 above, the Minister may cancel, the license based on the proposed decision submitted by the council and for one of the following reasons:
      (a) when the appropriate body proves that the license is acquired through fraudulent documents.
      (b) when the Health Professional is convicted for a serious crime which could indicate that one has no adequate competence to be considered as an ethical Health Profesional.
      (c) if found to have been deliberately working above one's capacity in contravention of the Health Professionals ethics.
      (d) if found to have been rendering health services in return for an illegal benefit while suspended and in contravention of a written notice and a dicision of suspension.
5) without prejudice to what is generally stated in Article 19 (2) if service is terminated due to suspension or cancellation for criminal convictions and non-observance of ethics, the registry kept to this effect shall be open to the public. It shall also be published in a state-owned newspaper within 48 hours.
6) The Minister may issue health professionals ethical directives that may be of assitance in the implementation of these regulations.

## ክፍል ፭
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፳፭· **የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ግለሰብ ወይም ባለሙያ ወይም መሥሪያ ቤት ወይም የጤና ተቋም ወይም ምርመራ የያዘ አካል በዚህ ደንብ የተመለከተውን ተግባር ለማከናወን ከጤና ባለሙያ ጋር በተያያዘ መረጃ ሲጠየቅ የመተባበር ግዴታ አለበት።

፳፮· **ተፈጻሚነት ስለሌላቸው ህጎች**

ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም አሠራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

፳፯· **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥር ፲ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ.ም

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

## *PART 5*
## *Miscellaneous Provisions*

25. *Obligation to Cooperate*

Any individual or professional or office or health institute or an organ which is carrying out an investigation should in any way cooperate in providing information related to a Health Professional and that the duties which are mentioned in this regulations will be met.

26. *Inapplicable Laws*

No other regulation, directive or practice which is inconsistent with this regulations shall have effect with respect to mattes governed by these regulaitons.

27. *Effective Date*

These Regulations shall enter into force as of the date of their publication in the Federal Negarit Gazetta.

Done at Addis Ababa, this 18th day of January, 2002.

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF
THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE